የሰ/መ/ቁ. 47806

ታህሣሥ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- የሆህተሰማይ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት - ሻምበል አሰፋ ወልዴ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ዲያቆን አያሌው አዲሱ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥራ ውሌ ከሕግ አግባብ ውጪ ተቋርጦብኛል በማለት ተጠሪ የመሰረተውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ከሥራዬ ያላአግባብ አግዶኛል በማለት ሲሆን፣ ሲያገለግል የነበረውም በዲቁና እንደሆነ በክሱ ላይ ገልጾአል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከሥራው ሊሰናበት የቻለው የቤተክርስቲያንዋ ስሞነኛ ቁልፍ ያዥ ሆኖ በሰራበት እለት ከቤተመቅደስ ሙዳየ ምጽዋቶች ተሰብረው ተዘርፈዋል፡፡ ከዚህ የተነሣም ተጠሪ በወንጀል ተከሶአል፡፡ የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ክሱ ውድቅ እንዲደረግለት ጠይቆአል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣አመልካች ተጠሪን ወደ ሥራው እንዲመልስ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ሰርዞናል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 27 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት ሃይማኖታዊ ግንኙነት ነው፡፡ አመልካች በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት መሰረት የተቋቋመ ሃይማኖታዊ ተቋም ሲሆን፣ተጠሪ ደግሞ በዚህ ተቋም ውስጥ የሃይማኖት አገልግሎት እንዲሰጥ አባል ወይም ሰራተኛ የሆነ ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ሙዳየ ምጽዋቶች ተዘረፉ በተባለበት እለት ተጠሪ ቤተመቅደሱን መክፈቱንና በመቀጠልም ቅዳሴ እንደገባ በክርክሩ ገልጾአል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለውም በሐይማኖቱ ሥርአት መሰረት የሐይማኖቱ አገልጋይ በመሆኑ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ ክርክር ቀርቦለት በሰበር መ/ቁ. 18419 ግንቦት 4 ቀን 98 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የሐይማኖት ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የሥራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሚሸፈን አለመሆኑን በመግለጽ የሕግ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡ ከዚህ በኋላም በተመሣሣይ ጉዳዮች ቀርበው ቀደም ሲል በተሰጠው የሕግ ትርጉም እንደተሸፈኑ እየተገለጸ ሲወሰን ቆይቶአል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ሥልጣን ሳይኖራቸው ክርክሩን ተቀብለው ማስተናገዳቸው አግባብ አልነበረም፡፡ የሰጡት ውሳኔም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27517 ሰኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04821 ሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተው ክስ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረት የሚታይ ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን የሰሙት ስልጣን ሳይኖራቸው ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡

    መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ